

# የመንግስት እና የግል አጋርነት ፖሊሲ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ነሐሴ 2009 ዓ.ም.

የገንዘብና ኢኮኖሚ
ትብብር ሚኒስቴር

# ማውጫ


1. መግቢያ ........ 1
2. የፖሊሲው መነሻዎች ........ 4
   - የአገሪቷን ሩዕዩና የልማት ዕቅድ እንደ መነሻ ........ 4
   - የመሰረተ ልማት አቅርቦት ፍላጎት እንደ መነሻ ........ 5
   - የአገሪቱ የኢንቨስትመንት ፍላጎት እንደመነሻ ........ 6
   - የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ መኖር እንደ መነሻ ........ 7

3 የመግለ ግቦችና ዓላማዎች ........ 8
   - ግቦች ........ 8
   - ዓላማዎች ........ 8

4 የፖሊሲው መርሆዎች ........ 11

5 የተፈፃሚነት ወሰን እና አጠቃቀም ........ 16
   - የመንግስት እና የግል አጋርነት ትርጓሜ ........ 16
   - የፖሊሲው የተፈፃሚነት ወሰን ........ 17
   - የመግለ ፕሮጀክቶች መምረጫ መስፈርቶች ........ 17

6 የአስተዳደር ማዕቀፍ ........ 22
   - የመግለ ተቋማት ሚና እና ኃላፊነት ........ 22
   - የመንግስት ተሳትፎ እና ድጋፍ ........ 26
   - የመግለ ሂደት ........ 28

# 1 መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ መንግስት ፈጣን፣ መሠረተ-ሰፊ፣ ዘላቂ እና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ዕድገት በማረጋገጥ አገሪቱን በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለማሰለፍ የልማት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች እና ፕሮግራሞችን ቀርጾ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡ ባለፉት ዓመታት ተቀርጸው በመተግበር ላይ የሚገኙት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች እንዲሁም ፕሮግራሞች ውጤት በማስገኘታቸው የአገራችን ኢኮኖሚ ላለፉት አሥራ አራት ዓመታት በአማካይ በየዓመቱ የሁለት አኃዝ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ ይህ ውጤት የተመዘገበው በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ("ዕትዕ-1") የተጀመሩት በርካታ ፕሮጀክቶች በአብዛኛው በተሳካ ሁኔታ የተተገበሩ በመሆኑ ነው፡፡ በተመሣሣይ መልኩ በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድም ("ዕትዕ-2") የተቀረጹትን ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች ለማስፈጸም መንግሥት ከፍተኛ ገንዘብ መድቦ ለአፈጻጸሙ ሲረባረብ ቆይቷል፡፡ ይህም ሆኖ የህዝብ አገልግሎቶች አቅርቦት በመጠንም ሆነ በጥራት ይበልጥ ሊጠናከርና ሊሟላ የሚገባው በመሆኑ በቀጣይም ከፍተኛ መጠን ያለው ኢንቨስትመንት እንደሚያስፈልግ ታይቷል፡፡ በሌላ በኩል ግን የመንግስት ዘርፍ ብቻውን የሚፈለገውን ፋይናንስ ለማቅረብ የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም፡፡

ስለሆነም አገሪቱ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ ያስቀመጠችውን ራዕይ ለማሳካት ከዚህም ጋር ተያይዞ በየጊዜው ሳያቋርጥ እያደገ የመጣውን የህዝብ አገልግሎት ፍላጎት ለማሟላት ከመንግስት የፋይናንስ ምንጮች በተጨማሪ ሌሎች አማራጮችን ማፈላለግ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ከነዚህ ተጨማሪ ምንጮች መካከል የመንግሥትና የግል አጋርነት አንዱ ስልት እንዲሆን ተመርጧል፡፡ የመሰረተ-ልማት የፋይናንስ ጉድለትን ለማሟላት የግሉን ዘርፍ በአጋርነት ማሳተፍ እንደ አንድ የመፍትሄ ስልት መታየት ከተጀመረ ቆይቷል፡፡ የመንግስትና የግል አጋርነት (መግአ) የመሰረተ-ልማት አቅርቦትን ለማሻሻል እንደ አንድ ስልት ወይም ዘዴ የሚወሰድ ሲሆን በአግባቡ ሥራ ላይ ከዋለ የግሉን ዘርፍ የኢንቨስትመንት አቅም እንደ አስፈላጊነቱ እንዲጠቀምበት ዕድል የሚሰጥ ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ከግል ዘርፉ ጋር እንዲኖር የሚፈልገውን አጋርነት እውን ለማድረግ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የመንግስትና የግል የአጋርነት ፕሮግራም እንዲነድፍ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ ይህ የመግአ ፖሊሲ የአጋርነቱ የአጠቃቀምና የትግበራ ፖሊሲ ሲሆን የህግ ማዕቀፍ የማዘጋጀቱ ሥራ የመጀመሪያና ወሳኝ እርምጃ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ ፖሊሲ የመግአ ፕሮጀክቶች በመላ አገሪቱ የሚተገበሩበትን ሁኔታ በተመለከተ አቅጣጫ የሚሰጥ እንዲሁም የመግአ አፈጻጸም የሚመራበት ሰነድ ከመሆኑም ባሻገር የመንግስትና የግል አጋርነት ወጥ በሆነ መልክና በግልጽነት እንዲተገበር ይረዳል፡፡

የመግአ ማዕቀፍ የመንግስትና የግል አጋርነትን ለማሳለጥ የሚረዱ የአሠራር ሰነዶችንና የአስተዳደር መዋቅርን የሚያካትት ይሆናል፡፡ የመግአ ሽፋንና አጠቃቀምን፣ የመግአ ፕሮጀክቶች አመራረጥንና አዘገጃጀትን፣ የቁልፍ ተዋናዮች ማንነትና ሚና እንዲሁም እንደ አስፈላጊነቱ መግአን በተለየ ትኩረት እንዲከታተሉ የሚደራጁና የሚሰየሙትን ተቋማት የሚመለከቱ አዋጅችና እና ደንቦች በዚህ ማዕቀፍ የሚጠቃለሉ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመግአ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም የሚመለከቱ መመሪያዎች እንዲሁም የመግአ ቁልፍ ጉዳዮች የሚስተናገዱባቸው ዝርዝር ማኑዋሎች እና መደበኛ የመግአ የጨረታ ሰነዶች የዚህ ማዕቀፍ አካል ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

የመሰረተ-ልማት አቅርቦትን ፋይናንስ በማድረግ ረገድ መግአን እንደ አንድ አማራጭ መውሰዱ ለኢትዮጵያ አዲስ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያዎቹ ዓመታት መግአ ለሙከራ በተመረጡ ጥቂት የመሠረተ-ልማት ፕሮጀክቶች እንዲያተኩር ማድረጉ ተገቢ ይሆናል፡፡ እነዚህንም ፕሮጀክቶች በመመምረጥ ረገድ በሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ ቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው የመሰረተ-ልማት አውታሮች መጀመር ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ እነዚህ የሙከራ ፕሮጀክቶች ሲመረጡ ታሳቢ የሚደረገው የመንግስትን አቅም በመገንባቱ በኩል የሚኖራቸው አስተዋጽኦ እና ወደፊት መግአ በስፋት ለመተግበር ምርጥ ተሞክሮ ለመቀመር የሚያስችሉ መሆናቸው አንድ ዋነኛ ጉዳይ ነው፡፡ የመግአ ማዕቀፍ በኢትዮጵያ ሊቀስም የሚችለውን ተሞክሮ ሁሉ ባካተተ መልኩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጎለበተ እንደሚሄድ የሚጠበቅ ሆኖ ከዚህ ጎን ለጎን የአለም አቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎች ወሳኝ ባህርያትን ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚከናወን ነው፡፡ የዚህ ዋና ግብም ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ተሞክሮ እንድትጠቀም እና ከመነሻው ውጤታማ የሆነ፣ የመንግሥት ገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ የሚያስገኝ እንዲሁም መልካም አስተዳደር እና ግልጽነትን ያረጋገጠ የመግአ ፕሮግራም እንድትቀርጽ ለማድረግ ነው፡፡

በመሆኑም ኢትዮጵያ አጠቃላይ የልማት ዓላማዋን ለመደገፍ የመግአ ፕሮግራምን ለመተግበር ስትወስን የመግአ ፋይዳዎችን በውል በመረዳት እና ከዚሁ የሚገኙ ጥቅሞች ሳይሸራረፉ ተግባር ላይ ለማዋል የህግ ማዕቀፍ ማስፈለጉን በመገንዘብ ነው፡፡

# 2 የፖሊሲው መነሻዎች

## የአገሪቷን ራዕይና የልማት ዕቅድ እንደ መነሻ

ፈጣን፣ መሠረተ-ሰፊ፣ ዘላቂ እና ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ዕድገት ማረጋገጥ የኢትዮጵያ መንግስት ቁልፍ የፖሊሲ ዓላማ ነው፡፡ ይህ ዓላማ አገሪቱ በ2017 ዓ.ም. መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ የያዘችውን ራዕይ ለማሳካት የማይተካ ሚና ይኖረዋል፡፡ እንደሚታወቀው ከ1996 እስከ 2008 ባሉት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በአማካይ ከአስር በመቶ ያላነሰ ዕድገት ሲያስመዘግብ ቆይቷል፡፡ ይህንን ዕድገት ለማስቀጠል እና ዘላቂ ለማድረግ ብሎም የመዋቅር ሽግግር ለማምጣት አገሪቱ በስትራቴጂካዊ ዕቅድ እንድትመራ መደረጉ ጠቀሜታን አስገኝቷል፡፡

የሚጠበቀውን የኢኮኖሚ ዕድገትና መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት ትኩረት የሚሹ ቁልፍ ጉዳዮችን በሰባት ስትራቴጂካዊ ምሰሶዎች ሥር በማቀናጀት የመጀመሪያውን የአምስት አመት የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከ2002-2007 ዓ.ም. ተግባራዊ አድርጋለች፡፡ ምሰሶዎቹ ፈጣን እና ፍትሐዊ የሆነ የኢኮኖሚ ዕድገትን ማረጋገጥ፣ ግብርና ዋነኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ምንጭ እንዲሆን ማስቻል፣ ማህበራዊ ልማትን በተደርሽነትና ጥራት ደረጃ ይበልጥ ማበልጸግ፣ መልካም አስተዳደርን ማስፈን፣ የሴቶችና ወጣቶች ፍትሐዊ ተሳትፎን ማረጋገጥ እንዲሁም የማስፈጸም አቅም ማሻሻልን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በዚህም መሰረተ-ልማትን የማስፋፋት ዓላማ በዕቅዱ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶቷል፡፡ እነዚህንና ሌሎች ምሰሶችን የያዘው የመጀመሪያው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በአፈጻጸም ረገድ ብዙዎቹን የኢኮኖሚ፣ የመሰረተ ልማት እንዲሁም የማህበራዊ ዘርፍ ግቦችን በትግበራው የአምስት ዓመታት ወቅት አሳክቷል ፡፡

ሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ (ከ2008-2012) (ዕትዕ-2) በታህሳስ 2008 ዓ.ም. ፀድቆ ወደ ትግበራ ተገብቷል፡፡ ሁለተኛው የዕቅድ ሰነድ ከመጀመሪያው ጋር ሲነጻጸር በፖሊሲ አቅጣጫዎች በአብዛኛው ተመሳሳይ ትኩረት ይዞ ተቀርጿል፡፡ እንደ ዕትዕ-1 ሁሉ ዕትዕ-2 ለግብርና ዘርፍ ትኩረት የሚሰጥ ሲሆን የበለጠ የአምራች ኢንዱስትሪውን መሰረት ለማስፋት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣል፡፡ በመሆኑም ሌሎች ምሰሶዎች እንዳሉ ሆነው ዕትዕ-2 የሚከተሉትን ምሰሶዎች አካቶ ጸድቋል፡፡ እነዚህም የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ልማት፣ የመሰረተ ልማት ዕድገት እንዲሁም የግሉን ዘርፍ አቅም ማጎልበት ይጠቀሳሉ፡፡

በዚህም መሰረት እነዚህን ምሰሶዎች መሰረት ያደረጉ በርካታ ፕሮጀክቶች በሁለተኛው ዕትዕ ዘመን

ተቀርጸው በርካታዎቹ ወደ ትግበራ ገብተዋል፡፡ እነዚህ ፕሮጀክቶች የሚጠይቁት መዋለ ነዋይ፣ ቴክኖሎጂ እና ዕውቀት ከፍተኛ በመሆኑ መንግስት የግሉን ዘርፍ አቅም በሰፊው ለመጠቀም አቅዷል፡፡ ይህም እቅድ ተግባራዊ ከሚሆንባቸው መንገዶች አንዱ የመንግስት እና የግል አጋርነት እንደሚሆን ዕቅዱ አመላክቷል፡፡ በመሆኑም የመንግስትና የግል ሽርክና አሠራርን በመተግበር የአገሪቷን የመሠረተልማት ፍላጎት በመሙላት ኢኮኖሚያችን በቀጣይ ለማሳደግ የሚረዳ መሆኑ ታምኖበት ይህ ፖሊሲ ተዘጋጅቷል፡፡

## የመሰረተ ልማት አቅርቦት ፍላጎት እንደ መነሻ

የኢትዮጵያ የልማት ፖሊሲዎችና እስትራቴጂዎች በመሰረተ ልማት እና በኢኮኖሚ ዕድገት መሃከል ላለው ቁርኝት እና መስተጋብር ግልጽ እውቅና በመስጠት የተቃኙ ናቸው፡፡ በመሰረተ ልማት የተሻለ ተደራሽነት ሲኖር የኢኮኖሚውን ተወዳዳሪነት በማሻሻልና ከፍ ያለ የግል ዘርፍ ምርታማነትን በማረጋገጥ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማፋጠን ያስችላል፡፡ በፊዚካል መሰረተ ልማቶች ላይ መዋዕለ ንዋይ ማፍሰስ የማምረቻ ወጪን በመቀነስ፤ የዕቃዎችንና አገልግሎቶችን እንዲሁም የሰዎችን እንቅስቃሴ በማቀላጠፍ ረገድ ያለው ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያከራክር አይደለም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በማህበራዊ መሰረተ-ልማትና ሌሎች የህዝብ አገልግሎቶች ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት የትምህርትና የጤና አገራዊ ውጤቶች እንዲሻሻሉ በማድረግ ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ አለው፡፡ የመሠረተ ልማት መስፋፋትና የጥራት መሻሻል በተለይ እንደኢትዮጵያ ላሉ ዝቅተኛ የመሠረተ ልማት ሽፋን ላላቸው አገሮች ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆን ከእስከአሁኑ የልማት ጥረትም የታየ ጉዳይ ነው፡፡

በኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ረገድ ያለውን ሚና ጠንቅቆ በመገንዘብ ሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሰረተ-ልማትን እንደ አንድ ስትራቴጂካዊ ምሰሶ እውቅና እንዲሰጠው አድርጓል፡፡ በዚህ ዕቅድ ውስጥ የተካተቱት የመሰረተ ልማት ዝርጋታዎች የመንገድ ግንባታ፣ የምድር ባቡር መስመር እና የሎጂስቲክስ አገልግሎቶች ግንባታ፣ አዳዲስ የአውሮፕላን ማረፊያዎች ግንባታ፣ የኃይል ልማት፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማስተላለፊያና ማከፋፈያ፣ የውኃ አቅርቦት እና ሳኒቴሽን አገልግሎቶች እና የመስኖ መሠረተ-ልማት ግንባታዎችን ይጨምራል፡፡

ከማስፈጸም አንፃር ግን የመሠረተ ልማት ሥራዎች የሚጠይቁት አቅም ከፍተኛ ነው፡፡ በተለይ በፋይናንስ ረገድ ከፍተኛ አቅምን የሚፈልጉ ሲሆን ከዕድገት ደረጃ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ውስብስብ መሠረተ ልማቶች በቴክኖሎጂ እና በሰው ኃይል ዝግጁነት ረገድ ትልቅ አቅምን ይፈልጋሉ፡፡ ከአለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት የልማት ጥረት እንደታየው ኢትዮጵያ ከፍተኛ ድርሻ ያለውን የመንግሥት የፋይናንስ አቅም በመሠረተ ልማት ላይ ለማዋል የቻለች ቢሆንም የመሠረተ ልማት አገልግሎቶች አቅርቦት በስፋት እና በጥራት ረገድ ብዙ ሥራ እንደሚቀረው በግልጽ ይታያል፡፡ በዚህም ምክንያት የአገሪቱን ራዕይ ዕውን ለማድረግ የሚያስችል በቂ መጠን እና ጥራት ያለው የመሰረተ ልማት ዝርጋታን በመንግስት የፋይናነስ አቅም ብቻ ለማከናወን አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም የግሉ ዘርፍ በመሰረተ ልማት አቅርቦት ዘርፍ ያለውን

ተሣትፎ ለማስፋት የሚያስችሉ የተለያዩ እስትራቴጂዎች መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህም የመንግሥትና የግል አጋርነት አንድ ተጨማሪ እስትራቴጂ ሆኖ ይታያል፡፡

## የአገሪቱ የኢንቨስትመንት ፍላጎት እንደመነሻ

በሁለተኛው የዕድገትና የትራንስፎርሜሽን ዕቅድ የተያዙትን የልማት ውጥኖች ለማሳካት በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ ከ150 ቢልዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የሆነ ኢንቨስትመንት እንደሚያስፈልግ ተገምቷል፡፡ መካከለኛ ገቢ ካላቸው አገሮች ተርታ ለመሰለፍ ከዚሁ መጠን ያላነሰ ኢንቨስትመንት ከሁለተኛው የዕቅድ ዘመን ባሻገር ላለው ዘመንም ያስፈልጋል ተብሎ ይታመናል፡፡ ምንም እንኳን አብዛኛው ኢንቨስትመንት ከአገር ውስጥ ምንጮች እና የተወሰነው ደግሞ ከብድር ይገኛል ተብሎ የሚጠበቅ ቢሆንም የውጭ ኢንቨስትመንትንም ለመሣብና ለማንቀሳቀስ ከፍተኛ ጥረት እንደሚደረግ ሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ይጠቁማል፡፡

ኢንቨስትመንት በማበረታታት ረገድ ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን ይህን ዓይነት ኢንቨስትመንት በሚፈለገው መጠን እና ዓይነት ወደ ሀገር ውስጥ ከመሳብ አንፃር የመንግሥትና የግል አጋርነት (መግአ) አንዱ መሳሪያ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡ የመግአ ማዕቀፍ ትግበራ መንታ ዓላማዎች ያሉት ሲሆን፤ በአንድ በኩል የግል ዘርፉ በመሰረተ ልማት ላይ የሚያደርገው ኢንቨስትመንት የሚያበረታታ ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመሰረተ-ልማት አቅርቦትን ጥራት ለማሻሻል ያስችላል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን መግአ ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን የውጪ ካፒታል ፍሰት ይበልጥ ለማሳደግ እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማፋጠን እንደሚረዳ ይታመናል፡፡ የዕውቀት ሽግግር፣ የአገር ውስጥ የግል ዘርፍ አቅምን ማጎልበት፣ የኢንቨስትመንት ፍሰትን በማሻሻል የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ማሳደግ ከተጓዳኝ ዓላማዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የመግአ ፕሮጀክቶችና አጠቃላይ ፕሮግራሙ በሚተገበርበት ወቅት ይህ ፖሊሲና ፖሊሲውን ለማስፈፀም የሚዘጋጀው የህግ ማዕቀፍ እነዚህን ተጓዳኝ ዓላማዎች በሚፈለገው መጠን ከግብ ለማድረስ ያግዛል፡፡ በተለይም ይህ ፖሊሲ የመንግስትን ዓላማዎችና መንግስት ለመግአ የሰጠውን ትኩረት እና ያለውን ቁርጠኝነት በግልፅ በማሳየት ለአጋርነትው የሚያስፈልገውን ማዕቀፍ በጠንካራ መሰረት ላይ እንዲመሰረት ያደርጋል፡፡

## የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ መኖር እንደ መነሻ

በሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ከተያዙት ዋና ዋና ስትራቴጂዎች አንዱ ዕቅዱን በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ውስጥ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ ይህንንም ከግብ ለማድረስ ከሚያስችሉት ስልቶች መካከል ጤናማ የፊስካል ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን ለዚህም ዋነኛው የመንግስት የፊስካል ጉድለት ከማክሮ ኢኮኖሚው ዓላማ ጋር የተጣጣመ ማድረግ ሲቻል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በጥሩ ሁኔታ የተቀረጸ እና የተተገበረ የመንግሥትና የግል አጋርነት ፕሮግራም የህዝብ አገልግሎቶችን በማቅረብ ረገድ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ በማሳደግ በተጓዳኝ የመንግስት ወጪ እንዳይጨምር አስተዋፅዖ ያደርጋል፡፡

# 3 የመግለ ግቦችና ዓላማዎች

## ግቦች

ይህ ፖሊሲ የሚከተሉት ዋና ዋና ግቦች አሉት፡፡

- የህዝብ አገልግሎት ተግባራትን[1] ማስፋፋት፣
- የህዝብ አገልግሎት ተግባራት ወጪ ቆጣቢ እንዲሆኑ፣ በታቀደው ጊዜ እና ጥራት እንዲቀርቡ ማስቻል፣
- የግሉ ዘርፍ የህዝብ አገልግሎት ተግባራትን በማቅረብ ሃብቱን ስራ ላይ እንዲያውል ማመቻቸት ናቸው፡፡

## ዓላማዎች

### የመንግስትና የግል አጋርነት ዓላማዎች

መግአን በመጠቀም ፕሮጀክቶች መተግበር የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡፡

- ለአገራችን መሠረተ-ልማት ግንባታ እና አገልግሎቶች ማስፋፊያ የሚውለውን የፋይናንስ ሀብት ለማሳደግ እንዲቻል የግሉን ዘርፍ ኢንቨስትመንትና የስራ አመራር ክህሎት መጠቀም፣
- ለግሉ ዘርፍ ድጋፍ በማድረግ እና የስጋት ኃላፊነትን እንዲጋራ በማድረግ የግሉ ዘርፍ በመሰረተ-ልማት ኢንቨስትመንት ይበልጥ ቢሳተፍ ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ማሳደግ ሌላው ዓላማ ነው፡፡ ከግል ዘርፍ ተሣትፎ ጋር የተያያዘው ጥቅም ሊገኝ የሚችለው ግን ተገቢ እና ትርጉም ያለው ስጋት ለግሉ ዘርፍ ማስተላለፍ ሲቻል ብቻ ነው፡፡ በስፋት የሚደረግ የግል ዘርፍ ተሣትፎ ሊያስገኝ የሚችላቸው ጥቅሞች በርካታ ሲሆኑ ከሚጠበቁት ጥቅሞች መካከል የሚከተሉት በዋነኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፤
- በመሠረተ-ልማት ዲዛይን በመሣተፍ ወይም የመሠረተ ልማት አገልግሎት በማቅረብ ረገድ ከግል ዘርፍ የሚመነጭ አዳዲስ የፈጠራ ሃሳቦችን (innovation) መጠቀም፣
- በፕሮጀክቶች አፈጻጸም ረገድ ሊኖር የሚችለውን የጊዜ መጓተትና የወጪ መናር መቀነስ፣
- የመሰረተ-ልማት አቅርቦት የዋጋ አተማመን የመሰረተ ልማቱን የሙሉ እድሜ ወጪ (life cycle approach) ግምት ውስጥ አስገብቶ እንዲሰላ ማመቻቸት፣

[1] በዚህ ፖሊሲ ውስጥ "የሕዝብ አገልግሎት ተግባር" ማለት በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ላይ በተቀመጠው መሠረት "ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ በመሆኑ እና በግል ዘርፍ ብቻ በብቃት ሊሰራ እንደማይችል የታመነበት በመሆኑ ምክንያት በመንግሥት የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ማለት ነው"፡፡

- የተሻለ ጥራት እና ቅልጥፍናን ማረጋገጥ፣
- ለአገር በቀል የግል ዘርፍ የዕውቀት ሽግግር ማመቻቸት፣
- ሀብትን (asset) በተሻለ ሁኔታ ለመጠቀም መቻል ናቸው፡፡

## የመንግስትና የግል አጋርነት ማዕቀፍ ዓላማዎች

ግልጽ በሆነ መንገድ አጠቃላይ አገራዊ ጥቅምን አይቶና የተፈፃሚነት ወሰን አበጅቶ በተዘጋጀ የፖሊሲና ህግ ማዕቀፍ መመራት በርካታ ጠቃሚነቶች እንዳሉት ይታመናል፡፡ መንግስት መግአን የመሰረተ-ልማት አቅርቦት ስልት አድርጎ መውሰዱ በተመረጡ ፕሮጀክቶች በመጀመር መተግበሩ የፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ከማሳለጥ ባሻገር የግል ዘርፍ ልምድ እና ኢንቨስትመንት አቅምን በመጠቀም ወደፊት በርካታ የህዝብ አገልግሎቶችን በስፋት ለማቅረብ ያስችላል፡፡ መግአን በሰፊው በመተግበር ሊገኝ የሚችለውን ጥቅም ለማረጋገጥ በረዥም ጊዜ እንዲሁም ቀስ በቀስ በሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፎች የፕሮግራም ስልትን ለመከተል እና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል አቅጣጫን ያመቻቻል፡፡ የመግአ ፕሮጀክቶች አቀራረጽና አተገባበር ስልትም በመግአ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲካተት ይደረጋል፡፡ በዚህ ላይ መግአን ሥራ ላይ ለማዋል የመግአ ፕሮጀክቶች የሚቀረጹበት ሂደት የሚመራበት የመግአ ፖሊሲ፣ የማስፈጸሚያ አዋጅ እና ዝርዝር መመሪያዎች መኖራቸው ለመግአ ፕሮግራም አፈጻጸም ስኬት ወሳኝ ነው፡፡

ይህንን ስልት መከተል የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡፡

- የግሉ ዘርፍ በመሠረተ-ልማት ኢንቨስትመንት ውስጥ ያለውን ተሳትፎ ለማሳደግ አስቻይ አካባቢያዊ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ በመግአ ፕሮጀክቶች አተገባበር ዙርያ ከአገር ውስጥም ሆነ ከዓለም አቀፍ የግሉ ዘርፍ ተሳታፊዎች የሚመነጨውን ዕውቀት በማደራጀትና በሰፊው በማጋራት፣ ስኬታማ የመግአ አዘገጃጀት ሞዴል በአገሪቱ እንዲኖር ማድረግ፣
- ከመግአ አንፃር ለሁሉም የመንግስትና የግል ዘርፍ ተሳታፊ ወገኖች የሚሰጠው ኃላፊነት ተገማችና ግልፅ እንዲሆን ማድረግ፣
- በመግአ ቀረጻ፣ አፈጻጸም እና ቁጥጥር መስከ የግል ዘርፍ አጋርን መምረጥ ጨምሮ ያሉትን ሂደቶች በተመለከተ ተገቢውን አመራር በመስጠት ለማስተባበር፣ እንዲሁም
- ተጨባጭ የመግአ መገምገሚያ ስርዓት በማበጀት በቀጣይ የመግአ ማዕቀፍ በኢትዮጵያ የሚጎለብትበትን እና የመግአ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም የሚጠናከርበትን መንገድ ማመቻቸት ናቸው፡፡

# 4 የፖሊሲው መርሆዎች

መንግስት ለመሰረተ-ልማት መስፋፋት እና ለህዝብ አገልግሎቶች ፍላጎት መሟላት ቁርጠኝነት አለው፡ ፡ ይህንን በማሟላት ረገድ የግል ኢንቨስትመንትን ጨምሮ ሊገኝ የሚችለውን ሃብት በተሻለ መንገድ ለመጠቀም የሚያስችለውን ማናቸውንም ስልት በመቀየስ ስራ ላይ ያውላል፡፡ የመሰረተ-ልማት አቅርቦት ስልት የመምረጥ ስራ የሚከናወነው የትኛው ስልት ሊያጋጥሙ የሚችሉትን እጥረቶች ወይም መሰናክሎችን በብቃት ተቋቁሞ የህዝቡን የልማት ፍላጎት በተሻለ ሁኔታ ለሚሟላት ያስችላል ለሚል ጥያቄ አጥጋቢ መልስ መስጠት የሚያስችል መሆኑን በማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ብዙ ታሳቢዎችን ማጤን የሚጠይቅ ሲሆን መንግስት የመግአ ማዕቀፍን ሲያዘጋጅና የመግአ ፕሮጀክቶችን ሲያስፈጽም ለሚከተሉት መርሆዎች ተገዥ ይሆናል፡፡

## የህዝብን ጥቅም ማስጠበቅ

ከላይ እንደተጠቀሰው በመግአ አማካኝነት የሚቀረቡ የሕዝብ አገልግሎቶች የመንግሥት ኃላፊነት እና ትኩረት የሆኑ አገልግሎቶችን ስለሚሸፍኑ በዜጎች የዕለት ተዕለት ኑሮ ላይ የሚኖራቸው ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡ የእነዚህ አገልግሎቶች አቅርቦት በወቅቱ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ እና ጥራት መሟላት ደግሞ በበኩሉ የመጨረሻ ተጠቃሚ የሆኑት ዜጎች የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ለሚደረገው ጥረት ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የእነዚህ አቅርቦቶች መሟላት ከቀጥተኛ ተጠቃሚዎች በተጨማሪ በአጠቃላይ የዜጎች ኑሮ መሻሻል ላይ አዎንታዊ ውጤት ይኖረዋል፡፡

ፕሮጀክቶች በአካባቢ ላይ የሚያሳድሩትን አሉታዊ ውጤትና ተጽዕኖ ለመቀነስና ለመቆጣጠር መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች ይኖራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለህዝቡ አገልግሎት ለማቅረብ የሚያስፈልጉ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶች ትግበራም ሆነ ራሱ አገልግሎት የመስጠት ሂደት ውስጥ በህዝብ ጤና፣ ደህንነት፣ የግለሰብ መብት፣ ለህዝብ በሚኖረው ተደራሽነት፣ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት እና በመሳሰሉት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ አበክሮ በማጤን ተፅዕኖውን መቀነስና መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተዘረዘሩትን ሃሳቦች መነሻ በማድረግ መንግስት መግአን በመተግበሩ ሂደት የህዝብን ጥቅም ምንጊዜም ታሳቢ የማድረግ ቁርጠኝነቱ አለው፡፡

## የግል ዘርፍ ተሳትፎ

በመሠረተ-ልማት አገልግሎቶች አቅርቦት ረገድ ቅድመ-ሁኔታዎች ከተመቻቹ እና በትክክል እስከ ተጠኑ ድረስ የግል ዘርፍ ተሳትፎ የሚያክለው የራሱ የሆነ እሴት መኖሩና መንግስት ለብቻው ከሚያደርገው አስተዋጽኦ በተጨማሪ ተጨባጭ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመናል:: በመሆኑም ተጨባጭ እሴት በሚታከልበት ዘርፍ ሁሉ የግል ዘርፍ ተሳትፎን ማበረታታት የመንግስት ግልጽ ፍላጎት ነው::

በመሰረተ-ልማት አቅርቦት የግል ዘርፉ ተሳትፎ መረጋገጥ ይኖርበታል ሲባል ለዚህ እምነት በርካታ መነሻዎችን መጥቀስ ይቻላል:: በተለይም የእሴት ጭማሪ የሚረጋገጥባቸው ሁለት ዓበይት መንገዶች ያሉ ሲሆን አንድም የሚቀርበውን አገልግሎት በማሻሻል ምክንያት የሚገኝ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በመሠረተ-ልማት ፕሮጀክቱ ትግበራና የዕድሜ ዘመን አፈፃፀም የሚገኙ የወጪ ቁጠባዎችን የሚመለከት ነው:: ከዚህም በላይ መንግስት የመግአ ፕሮግራምን በስፋት ለማራመድ የሚያስችል ልምድና የአሠራር ቅልጥፍና የሚያገኝበት ይሆናል:: ከዚህ ባለፈ በመግአ አማካኝነት የሚደረግ የግል ዘርፍ ተሣትፎ መንግሥት ለሚያራምደው አጠቃላይ የመሠረተ ልማት ፕሮግራም እና አጀንዳ ውጤታማነት የሚጨምረው እሴት እንደሚኖር ታሳቢ ያደርጋል:: የሚገኘው የእሴት ጭማሪ በሚከተሉት መልክ ሊሆን ይችላል::

ሀ. አንድን ፕሮጀክት በመግአ አማካኝነት መተግበር ሌሎች ተመሳሳይ ፕሮጀክቶች ሊገጥማቸው የሚችለውን የአጀማመርና አተገባበር ተግዳሮት ለማቃለል ይረዳል::

ለ. አንድ ፕሮጀክት በመግአ ስልት ሲፈጸም ለፕሮጀክቱ ሳይወጣ የቀረው የመንግሥት ፋይናንስ ለሌሎች የመግአ ፕሮጀክቶች ወይም ከዚህ ማዕቀፍ ውጭ ለሆኑ ፕሮጀክቶች ሊውል የሚችል መሆኑ የሚሉት ይጠቀሳሉ::

## የመግአ ፕሮጀክት አመራረጥ

በአጠቃላይ ከነባር የመሰረተ-ልማት አቅርቦት ስልት በተጓዳኝ የመግአ ስልትን መጠቀም ተጨማሪ ሌሎች ጠቀሜታዎችን ሊያስገኝ እንደሚችል የሚታመን ቢሆንም ይህ የሚሆነው ግን መግአ በአግባቡ የህብረተሰቡን የመሰረተ-ልማት ፍላጎት መሠረት አድርጎ ሲቀረጽና፣ ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ እና ችግሮችን ባገናዘበ መልኩ ሲታቀድ ነው:: በዚህም ምክንያት በመግአ ስልት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች የሚመረጡበት አካሄድ ከፍተኛ ትኩረት የሚፈልግ ጉዳይ ይሆናል:: ኢትዮጵያ በመግአ ስልት ልምድ የሌላት አገር በመሆኗ ደግሞ ሂደቱን በጥንቃቄ የመምራት አስፈላጊነትን ይበልጥ ወሳኝ ያደርገዋል:: በመሆኑም በመግአ ትግበራ የመጀመሪያ ዓመታት መንግስት ፕሮጀክቶች ሲመርጥ በጥቂትና የተወሰኑ ሴክተሮች ላይ ያተኮረ አነስተኛ መጠን ያላቸው ፕሮጀክቶች ላይ ሊያተኩር ይገባል:: እነዚህ ጥቂት ፕሮጀክቶች ሲመረጡም ቢሆን በተቻለ መጠን በመግአ ስልት መተግበራቸው ስኬት ሊያስገኙ እንደሚችሉ ሲታመን መሆን ይኖርበታል፡

፡ የመንግሥት የማስፈጸም አቅም እየዳበረ ሲሄድ በመግአ ስልት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶችን ቁጥርና ስብጥር እያሰፉ መሄድ ይቻላል፡፡

የትኞቹ ፕሮጀክቶች በመግአ ስልት መታቀፍ ይኖርባቸዋል የሚለውን ወሳኝ ጥያቄ መንግስት የሚመልሰው ግልጽ በሆኑ የመመዘኛና የመገምገሚያ መስፈርቶች ላይ በመመርኮዝ የተለያዩ የመሰረተ-ልማት አቅርቦት መንገዶችን በማጤንና የሚያስከትሉትን ወጪ እና የሚያስገኙትን ጥቅም በዝርዝር ካየ በኋላ ይሆናል፡፡ የዚህ አይነቱ ትንተና ሲካሄድ መንግስት ኃላፊነት የሚወስድባቸውን የስጋት ሁኔታዎች እንዲሁም እነዚህን የስጋት ሁኔታዎች በመምራት እና በማስተዳደር ረገድ ከጅምር እስከ ማጠናቀቂያ ድረስ በፕሮጀክቱ ወጪና የሰው ሃይል ላይ የሚኖረው አንደምታ መፈተሸና ታሣቢ ማድረግ የማይታለፍ ይሆናል፡፡ የዚህ ዓይነት ትንተና እና ግምገማ በተጨማሪ ሊዳስሰው የሚገባው ሌላው ጉዳይ በቂ የሚባል ስጋት ለግሉ ዘርፍ አጋሩ ስለመተላለፉ ለማረጋገጥ የሚያስችል ሊሆን ይሆናል፡፡ በዚህ መልክ ወደ ግሉ ዘርፍ የሚተላለፍ በቂ ስጋት ሲኖር በመግአው ተሣታፊ የሆኑት የመንግሥት እና የግል አካላት ፕሮጀክቱን ለመፈጸም የሚኖራቸው ፍላጎት እንዲጣጣም በማድረግ ለመንግሥት ተመጣጣኝ ገንዘብ ለማስገኘት ያስችላል፡፡

## የአስተዳደር ማዕቀፍ

መንግስት መግአን ሲጠቀም የመንግስት ሚናና ኃላፊነት የሆኑ የህዝብ አገልግሎቶች በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ ለግል ዘርፍ አጋር የሚተላለፉበት ሁኔታ ይፈጠራል ፡፡ እዚህ ላይ መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ አንድ ፕሮጀክት በመግአ አማካኝነት መተግበሩ ምንም ይሁን ምን መንግስት ለዜጎች የመሰረተ ልማት አገልግሎትን በማቅረብ ረገድ ያለበትን ግዴታና ተጠያቂነት አያስቀረውም፡፡ መንግስት ያለበትን ግዴታ ለመወጣት መግአን የአገልግሎት ማቅረቢያ የተቀላጠፈ ስልት አድርጎ ሊጠቀምበት ይችላል፡፡ ሆኖም ከአገልግሎቶች አቅርቦት ህብረተሰቡ የሚያገኘውን ውጤት እና ፋይዳ የማረጋገጥን ኃላፊነት በውክልና ለግል ዘርፍ ሊያስተላልፍ አይችልም፡፡ በዚህም ምክንያት በመግአ አተገባበር የግል ዘርፍን ሚና እና ኃላፊነት በመወሰን ረገድ መንግስት ወሳኝ ኃላፊነቶችን መወጣት ይጠበቅበታል፡፡ በተለይም በአንድ ወይም በሌላ ፕሮጀክት የግል ዘርፉ ሚና ምን ሊሆን እንደሚገባው ገደብ በማስቀመጥ እንዲሁም የግል ዘርፍን አጋር የስራ አፈጻጸም በተከታታይ በመገምገም ረገድ ቀጣይነት ያለው ስራ ማከናወን ይኖርበታል፡፡ ከእያንዳንዱ ፕሮጀክት አፈጻጸም በተጨማሪ መንግስት የመግአ ፕሮጀክቶችን ለማጥናትና ለማዘጋጀት የሚያስፈልገውን ወጪ መመደብ ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም መግአ እንደ ስልት በሚመርጥበት ጊዜ ከተለያዩ ፕሮጀክቶች በአገር ደረጃ በዚህ ስልት የሚገኘውን አጠቃላይ ጥቅም መንግስት በተለመደው የግዢ አኳኋን ከሚያወጣው ወጪ ወይም ሃብት ጋር በማነጻጸር የሚኖረውን ልዩነት በሚገባ በማመዛዘን ውሣኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

## የግል ዘርፍ አጋር አመራረጥ

መግአ በረዥም ጊዜ የኮንትራት ስምምነት ወሳኝ የሆኑ የመሠረተ-ልማት አገልግሎቶችን ለህብረተሰቡ ማቅረብ የሚያስችል በመሆኑ ከዚህ የመግአ ልዩ ባህሪ  የተነሳ መግአን ውጤታማ ለማድረግ የግል ዘርፍ አጋር አመራረጥ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በዚህ ረገድ መንግስት በመግአ ለሚታቀፉ የተለያዩ ባህርያት ላላቸው ፕሮጀክቶች የግል አጋር ለመምረጥ የተለያዩ ፈጠራ የታከለባቸው ዘዴዎችን መጠቀም ያለበት ሲሆን፣  ግልጽ፣ ወጥ፣ የማያሻማ፣ እና ውድድርን የሚያበረታታ የግል አጋር አመራረጥ ስርዓት መዘርጋት ይጠበቅበታል፡፡ በመሆኑም ለመግአ የሚዘጋጀው ማዕቀፍ የመግአ አጋርን ለመምረጥ የሚያስፈልጉ ህጋዊ መሠረቶችን እና የመግአ ግዥ ሥርዓቶችን እንዲያስቀምጥ ይጠበቃል፡፡ ከዚህም በላይ ብቁ የሆነ የግል ዘርፍ አጋር በመምረጥ በኩል ማዕቀፉ የተሟላ መረጃ ይሰጣል፡፡

# 5 የተፈፃሚነት ወሰን እና አጠቃቀም

የመግአ ማዕቀፍ እንዲያብራራቸው ከሚጠበቁ ጉዳዮች መካከል ፖሊሲው የየትኞቹ መንግሥታዊ ተቋማት አማካኝነት በሥራ ላይ እንደሚውሉ፣ እንዲሁም በመግአ አማካኝነት የሚተገበሩ ፕሮጀክቶች ዓይነትና ይዘት በዋነኝነት ይጠቀሳሉ፡፡ በዚህም መሠረት ይህ የፖሊሲው ንዑስ ክፍል በማዕቀፉ የሚሸፈኑት መንግስታዊ ተቋማት እነማን ሊሆኑ እንደሚችሉ ይጠቁማል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ፖሊሲው በማዕቀፉ ውስጥ ለመካተት ምቹ የሚሆኑ የፕሮጀክት ዓይነቶች የትኞቹ እንደሆኑና በዚህ ማዕቀፍ ውስጥ ለመካተት ማሟላት የሚኖርባቸውን ዋና ዋና መስፈርቶች ይጠቁማል፡፡

## የመንግስት እና የግል አጋርነት ትርጓሜ

በዚህ የፖሊሲ ሰነድ ለመንግስት እና የግል አጋርነት (መግአ) የተሰጠው ትርጉም በተዋዋይ ባለስልጣን እና በግል አጋር መካከል የሚደረግ የረዥም ጊዜ ስምምነት ሆኖ፣

- የግል ዘርፍ የህዝብ አገልግሎት ተግባራትን የሚያቀርብበት ወይም ለህዝብ አገልግሎት ተግባራት አቅርቦት አስተዋጽኦ የሚያደርግበት፣
- የግል ዘርፍ ለሚያቀርበው አገልግሎት ከመጨረሻ ተጠቃሚዎች በክፍያ መልክ ወይም ከመንግስት በጀት ወይም በሁለቱም መንገዶች በጣምራ ገቢ የሚያገኝበት ሲሆን፣
- የግል ዘርፍ በመግአ አማካኝነት የሚያገኘው ገቢ የሚመሰረተው ውለታ የተገባለት አገልግሎት በውለታው መሰረት በብዛትና በጥራት መቅረቡ ሲረጋገጥ ብቻ ይሆናል፡፡ በዚህም የክፍያ እንዲሁም ስጋት ድልድል አረጃጀት መሠረት የህዝብ አገልግሎት በማቅረቡ ሂደት ትርጉም ያለው የስጋት ድልድል ለግል ባለኃብቱ መተላለፉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

## የፖሊሲው የተፈፃሚነት ወሰን

ለሕጉ ተገዢ መሆን ያለባቸው ተዋዋይ ባለስልጣናት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በሙሉ ወይም በከፊል በመንግስት በሚመደብ በጀት የሚተዳደር የፌዴራል መንግስት ተቋም፣ እና፣
- ማናቸውም ሙሉ በሙሉ ወይም በአብዛኛው በፌዴራል መንግስት ባለቤትነት የተያዘ እና የመግአ ትርጓሜን ያሟላ ፕሮጀክት የሚያካሂድ የመንግስት የልማት ድርጅት ናቸው፡፡

- የክልል መንግስታት ይህንን ፖሊሲ መሠረት በማድረግ የራሳቸውን የአሠራር ማዕቀፍ መዘርጋት ይችላሉ፡፡

## የመግአ ፕሮጀክቶች መምረጫ መስፈርቶች

በተዋዋይ ባለስልጣን የሚካሄዱ ፕሮጀክቶች በዚህ ፖሊሲ ውስጥ የተቀመጠውን አጠቃላይ የመግአ ትርጉም የሚያሟሉ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ የመግአ የአተገባበር ስልት እንዲጠቀሙ ከመወሰኑ በፊት ይህ ስልት ከሌሎች ስልቶች የተሻለና አግባብነት ያለው መሆኑ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ልዩ ልዩ ፕሮጀክቶች በመግአ ስልት ሊተገበሩ የመቻላቸውን ያህል፣ በዚህ ስልት ፕሮጀክቶችን ለመተግበር መቻሉ ብቻ የመግአ ስልት ለእነዚህ ፕሮጀክቶች ከሁሉም ስልቶች የተሻለ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ያስገኛል ማለት ስለማይቻል በአመራረጡ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል፡፡ በተለይም በመንግስት አቅም እና ልምድ ውስንነት ምክንያት በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የማዕቀፉ ትግበራ በአንድ ጊዜ በርካታ ፕሮጀክቶችን ለመንደፍና ለመምራት የሚያስችል አይሆንም፡፡ ከዚህም የተነሳ ከሁሉም አስቀድሞ በመግአ ስልት አማካኝነት ሊተገበሩ ይችላሉ ተብለው የታጩ ፕሮጀክቶች የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላታቸው በዝርዝር መገምገም ይኖርበታል፡፡ ከዚህ አንፃር ለመግአ ብቁ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን ለመምረጥ የሚያገለግሉ ቁልፍ መስፈርቶች ከዚህ በታች ቀርበዋል፡፡ በዚህ ፖሊሲ ሰነድ የተቀመጡት መሥፈርቶች ጥቅል ሲሆኑ በተጨማሪም የዚህ አይነቱን ግምገማ እንዴት ማካሄድ እንደሚቻል የሚያስረዳ ዝርዝር መመሪያ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

## ሀ. ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ ማስገኘት (Value for Money)

የመሰረተ-ልማት አቅርቦትን በተመለከተ በፖሊሲው መርሆዎች ላይ እንደተገለጸው በመግአ ስልት የመፈጸም አግባብ የሚሆነው መንግስት ብቻውን ሊፈጥረው ከሚችለው እሴት በላይ የግል ዘርፍ ተሳትፎ ሲታከል ሊፈጠር የሚችለው እሴት ተመጣጣኝ ወይም የላቀ ሲሆን ነው፡፡ ይሁን እንጂ የግል ዘርፍ ተሳትፎ መኖሩ በራሱ ተጨማሪ እሴት ይፈጥራል የሚል ዋስትና ሊያስገኝ አይችልም፡፡ በአጠቃላይ ግን የግል ዘርፍ ቢሳተፍባቸው በቂ እሴት ከማመንጨታቸው የተነሳ በመግአ በኩል መተግበራቸው አሳማኝ ነው የሚባሉት ፕሮጀክቶች ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ የሚያስገኙ መሆን አለባቸው፡፡ ይህንን በተጨባጭ ማረጋገጥ ደግሞ መግአን እንደ አንድ የመሰረተ-ልማት የአቅርቦት ስልት ለመቀበል በቅድመ ሁኔታነት ሊቀመጥ ይገባል፡፡

ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ መገኘቱ የሚሰላው አንድን ተጨባጭ ፕሮጀክት በመውሰድ የመግአ ስልት በመተግበር መንግስት የሚያወጣው ጠቅላላ የዕድሜ ዘመን ወጪ በነባር የአቅርቦት ዘዴ ወይም በመደበኛ የመንግስት ግዢ ሥርዓት ቢከናወን ሊያስከትለው ከሚችለው ጠቅላላ የዕድሜ ዘመን ወጪ ጋር በማነፃፀር ነው፡፡ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ መገኘቱን ለማስላት የተለያዩ የጥቅም እና የወጪ ግምቶችን መውሰድንም የግድ ይላል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን የእያንዳንዱ ፕሮጀክት ጥቅም እና ወጪ ሁሉን አቀፍ የሆነ ምዘና ማለትም የፋይናንስ እና ኢኮኖሚያዊ መመዘኛዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ መገኘቱን

እንዴት በዝርዝር ማስላት እንደሚቻል የሚያስረዱ ጠቋሚ ሃሳቦች በመግአ ማዕቀፍ መመሪያ ውስጥ የሚካተቱ ይሆናል፡፡

የስጋት ምንጮች በመንግስት እና በግል ዘርፍ መካከል የሚደለደሉበት አግባብ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ መገኘቱን ለማረጋገጥ በሚደረግ ትንተና ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አለው፡፡ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ መገኘቱ ይበልጥ ውጤታማ የሚሆነው የስጋት ድልድል ሲደረግ እያንዳንዱ የስጋት ምንጭ እና ተያያዥ ሁኔታዎችን በተሻለ ብቃት ለመቆጣጠር እና ለመቋቋም ለሚችል ተዋዋይ ወገን መተላለፍ ሲችል ነው፡፡ ይህም በፕሮጀክት ትግበራ ሂደት አጠቃላይ ወጪን በመቀነስ የመንግስትም የወጪ ድርሻ ዝቅ እንዲል ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ መገኘቱ ሲሰላ በፕሮጀክት ትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ የስጋት ሁኔታዎችንም ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ያህል መንግስት ወደ ግል ዘርፍ አጋር ከሚያስተላልፋቸው የስጋት ዓይነቶች ውስጥ ከታቀደው በላይ ወጪ ሊያስወጡ እንደሚችሉ የሚገመቱ ሆነው ነገር ግን በግል ዘርፍ ቢያዙ የተሻለ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚችሉትን በስጋት ክፍፍሉ ወደ ግል ዘርፍ እንዲተላለፉ ለማድረግ መሥራት ይኖርበታል፡፡ መንግስት በሙሉም ሆነ በከፊል ተሸክሚቸው የሚቀጥል የስጋት ዓይነቶች ለምሳሌ መንግስት የሚሰጠው የክፍያ ዋስትና በስሌቱ ግምት ውስጥ መግባት ካለባቸው ታሳቢዎች ውስጥ ይካተታሉ፡፡ እዚህ ላይ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባው ጉዳይ ማንኛውም ፕሮጀክት በመግአ ሥርዓት ሲተገበር ለመንግሥት ገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ ለማስገኘት የሚችለው በቂና ትርጉም ያለው ስጋት ለግል ዘርፍ ሲተላለፍ ይሆናል፡፡

የመግአ ፕሮጀክቶችን መንደፍና ማዘጋጀት ከፍ ያለ ወጪ የሚጠይቅ ስለሆነ፣ ትናንሽ ፕሮጀክቶችን በመግአ ስልት መተግበር ጠቃሚ ላይሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አንፃር ከአንዳንድ አገሮች ልምድም በመነሳት ጠቅላላ የኢንቨስትመንት ወጪያቸው ከ50 ሚልዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ የሆኑ ፕሮጀክቶች ብቻ በመግአ ስልት ለመተግበር የቅድመ ማጣሪያ ሆኖ እንዲያገለግል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ እንዲህም ሆኖ በልዩ ሁኔታ ጠቅላላ ወጪአቸው ከዚህ በታች ይሆናል ተብለው የሚገመቱ ፕሮጀክቶችም ቢሆኑ በመግአ የአቅርቦት ስልት ሊታቀፉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ በተለይም ፕሮጀክቶቹ ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ የማስገኘት አቅም እንዳላቸው በግልጽ ማሳየት ከተቻለ በመግአ ማዕቀፍ ውስጥ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

## ሰ. የመክፈል አቅም

የመግአ ስምምነቶች በአብዛኛው መንግስትን በረጅም ጊዜ ግዴታ ውስጥ የሚያስገቡ፣ ወይም ተጠቃሚዎች ለሚያገኙት አገልግሎት ለግል ዘርፍ ክፍያ እንዲፈፅሙ የሚያስገድዱ፣ ወይም ሁለቱ ግዴታዎች አንድ ላይ እንዲፈጸሙ የሚያመቻቹ ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት የገቢው ወይም የክፍያው ምንጭ ምንም ይሁን ምን መንግስትና የአገልግሎቱ የመጨረሻ ተጠቃሚ ዜጎች የመክፈል አቅምን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ፕሮጀክቶችን በመግአ ስልት ለማስፈጸም የሚደረጉ ጥናቶች በጥንቃቄ ላይ በተመሰረተ ትንተና የታሪፍ ወይም የመንግስት በጀት ድልደላ ትንበያ እንዲካሄድላቸው ይጠበቃል፡፡ ከዚህ ትንበያ በኋላ ፕሮጀክቶች መገምገም ያለባቸው ከመጨረሻ ተጠቃሚ ዜጎች የመክፈል አቅምና ፍላጎት እና/ወይም

ከመንግስት የበጀት አቅም አንጻር ነው፡፡ በመጨረሻም የተጠቃሚ ዜጎች የመክፈል አቅምና ፍላጎት አነስተኛ ወይም የተገደበ ሆኖ ከተገኘ የመንግስትን በጀት በደጋፊነት በመጠቀም እንደ አግባብነቱ የተጠቃሚዎችን ታሪፍ የመቀነስ ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡

## ሐ. የህዝብ ጥቅም

መንግስት የዜጎችን መብትና ጥቅም የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለበት እንደመሆኑ፣ የመግአ ፕሮጀክቶች የዕድሜ ዘመን አፈፃፀም በህዝብ ጥቅም ላይ ምን ተጽዕኖ ሊያሣርፍ እንደሚችል በሚገባ ለመረዳት እያንዳንዱ ፕሮጀክት በዝርዝር መጠናት አለበት፡፡ ይህም ማለት አንድ የህዝብ አገልግሎት ማቅረቢያ ስልት ሲቀረጽ እና ለዚሁ የሚያገለግለው ፕሮጀክት በመግአ ስልት አማካኝነት ከመተግበሩ በፊት ፕሮጀክቱ በአካባቢያዊ፣ በህዝብ ጤና እና በደህንነት እንዲሁም በአጠቃላይ በምልአተ ህዝቡ እና በአገልግሎቱ የመጨረሻ ተጠቃሚዎች የኑሮ መሻሻል ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ ነው፡፡ እነዚህ ተጽዕኖዎች በጥልቀት ተተንትነው ለመንግስት ውሣኔ መቅረብ አለባቸው፡፡  ይህ መሆኑ መንግስት በበቂ መረጃ ላይ ተመስርቶ በፕሮጀክቱ ዙርያ የኢትዮጵያን ህግ መሰረት በማድረግ ለዜጎች የተሟላ ደህንነት እና ፍትሃዊ ጥቅም መጠበቅ መሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎችና ዝግጅቶችን አስመልክቶ ጥናት እንዲደረግ እንዲሁም በዚህ ጥናት መሠረት ውሣኔ የሚሹ ጉዳዮች ተለይተው ለመንግስት ውሳኔ እንዲቀርቡ እና ውሣኔ የሚሰጥበት ሁኔታ መፈጠር ይኖርበታል፡፡

## ሠ. ዘላቂነት

የመግአ ስምምነቶች የረዝም ጊዜ ስምምነቶች ከመሆናቸው ምክንያት፣ ከፕሮጀክቶቹ በሚጠበቁም ውጤቶች ይሁን በሂደት በድንገት በሚከሰተ ሁኔታዎች ሳቢያ በረዥሙ ሂደት ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉትን ለውጦች፣ መዋዣቆች እና የውጤት መዛባቶች በሚገባ ለማስተካከልና ለመቋቋም በሚያስችል ሁኔታ ዲዛይን ሊደረጉ ይገባል፡፡ በተቻለ መጠን የመግአ ስምምነቶች ሲረቀቁና ድርድር ሲደረግባቸው ሁሉም ወገኖች ለተለዋዋጭ ሁኔታ ራሳቸውን በተገቢው ደረጃ እንዲያዘጋጁ ማስቻላቸውን ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡ ሆኖም ከሁሉም በላይ ለዘላቂነት ዋስትና የሚሰጠው በፕሮጀክቱ የተፈጠረው መሠረተ-ልማት በአገልግሎት ዘመኑ በሙሉ ለሁለቱም ወገኖች ጥቅም ማስገኘት ሲችል ነው፡፡ ሁለቱም ወገኖች ከስምምነቱና ከመስተጋብሩ እንደሚጠቀሙ ሲገነዘቡ፣ ሁኔታዎች ምንም ተለዋዋጭ ቢሆኑ የስምምነቱን መንፈስ ለመጠበቅ ይተጋሉ፡፡ ይህ ሁኔታ፣ የመሰረተ-ልማቶች የአቅርቦት ጥራት እና ዋጋ ላይ ማተኮር ብቻውን በቂ ግብ ሊሆን እንደማይችል ያሣያል፡፡ ይልቁንም የግል ዘርፉ የተሸከመውን የስጋት ሁኔታ ያገናዘበ ተገቢ ትርፍ ማግኘት እንደሚገባው መንግስት አጥብቆ ማመን ይኖርበታል፡፡ ፕሮጀክቶች ሁሉም ወገን ተጠቃሚ በሚሆኑበት መንገድ እንዲቀረጹ ማድረግ የግል ዘርፉ አጋር ለፕሮጀክቱ መሣካት የሚኖረውን ጉጉት ከፍ ከማድረጉም በላይ በውድድር ላይ የተመሰረተ የግል ዘርፍ አጋር መረጣ እንዲኖር የሚያበረታታና ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ የመስገኘቱን ዕድል የሚያሻሽል ይሆናል፡፡

## ሠ. ተቋማዊ ጠቀም

የመግአ ስምምነቶች ውስብስብ እና ለማዘጋጀት ሰፊ ጊዜ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በመንግስት ላይ የረዥም ጊዜ ግዴታን የሚያስከትሉ ሲሆን እነዚህ ግዴታዎች በሁለት ሰፋፊ ፈርጆች ይመደባሉ፡፡

- በስምምነቱ የተቀመጡ ከመንግስት የሚጠበቁ ግዴታዎችን መፈጸም፤ ከነዚህም መካከል መሬት ማቅረብ፣ ከመሰረተ-ልማት ጋር ማገናኘት፣ ክፍያዎችን በወቅቱ መፈጸም፣ ታሪፎችን እየተከታተሉ ማሻሻል እና፣
- የግል ዘርፍ አጋሩአጋሩ በስምምነቱ መሰረት ግዴታዎችን ስለመወጣቱ ለማረጋገጥ ወቅታዊና ተከታታይነት ያለው የአፈጻጸም ክትትል ማድረግ ናቸው፡፡

ለመንግሥት ገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ ማስገኘት ከሚመሰረትባቸው ነጥቦች መካከል አንዱ ለፕሮጀክቱ ዝግጅት የሚደረገው በቂ ዝግጅት፣ ጥራትና ቅንቃቄ ሲሆን ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ መንግስት በስምምነቱ የገባባቸውን ግዴታዎች በተሟላ ሁኔታ ለመወጣት መቻሉ ይጠቀሳሉ፡፡ በመሆኑም በፕሮጀክት ቀረጻ እና ዝግጅት ወቅት እንዲሁም በመላ የፕሮጀክቱ የዕድሜ ዘመን የሚያስፈልገውን ተቋማዊ አቅም በሚገባ መገንዘብ በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ መንግስታዊ ተዋዋይ ባለስልጣን እነዚህን የመጪ ጊዜ ግዴታዎችን በምን ያህል ብቃትና ችሎታ መወጣት እንደሚችል መተንተኑ የመግአ የግዥ ስልትን እንደ አንድ የአቅርቦት ስልት በመምረጥ እና ባለመምረጥ ሂደት ራሱን የቻለ አንድ የመምረጫ መስፈርት መሆን ይኖርበታል፡፡

# 6 የአስተዳደር ማዕቀፍ

የመግአ ፕሮጀክቶችን ስኬታማ በሆነ መንገድ በመንደፍ፣ በመገምገም፣ በመፈጸም እንዲሁም በመከታተል ረገድ መንግስት በርካታ የማስተባበር እና ቅንጅት ስራዎችን ማከናወን ይኖርበታል፡፡ የመግአ ማዕቀፍ የሚፈለግበት አንዱ ዋና ምክንያትም የአሰራር ወጥነት ለማስፈን እና የተለያዩ ወገኖች ሚናና ኃላፊነት ግልጽ በሆነ መንገድ ለማስቀመጥ እንዲሁም እነዚህ ወገኖች በምን ዓይነት ሂደት አልፈው መቀናጀት እንዳለባቸው ለማሳየት ነው፡፡ ይህ የፖሊሲው ክፍል የመግአን ፕሮጀክት በመቅረጽ፣ በማዘጋጀት እና በመተግበር ሂደት ቁልፍ ኃላፊነቶች እና ሚናዎች የማን መሆን እንዳለባቸው ያሳያል፡፡ በዚህም መነሻነት የመግአ ሥርዓት አስተዳደር ማዕቀፍ ሰፋ ባለ መንገድ በአዋጅ፣ መመሪያዎች እና በሌሎች ሰነዶች ይብራራል፡፡

## የመግአ ተቋማት ሚና እና ኃላፊነት

### ሀ. የመግአ ቦርድ

የመግአ ቦርድ በፕሮጀክት ቀረጻ እና ዝግጅት ወቅት ወሳኝ በሆኑ እርምጃዎች ላይ የውሳኔ ሰጪነት ሚና የሚኖረው አካል ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ቦርዱ በመግአ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት የቀረቡትን የመግአ ፕሮጀክቶችን ዝርዝር መርምሮ ያጸድቃል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የመግአ ፕሮጀክቶች ለጨረታ እንዲቀርቡ ይፈቅዳል፡፡ በሦስተኛ ደረጃ ፕሮጀክቶች ለአሸናፊው ተጫራች እንዲሰጡና ስምምነት እንዲፈረም ይወስናል፡፡ በአጠቃላይም ቦርዱ ከላይ ከተገለጸው መሠረት ሲፈቅድና ሲያጸድቅ የፕሮጀክቱ አወቃቀር፣ በመንግስት ወገን እና በግል ዘርፍ አጋር በድርሻነት የሚወሰዱ የስጋት ሁኔታዎች አግባብነትና ትክክለኛነት፣ መንግስት ለፕሮጀክቱ የሚሰጠው ድጋፍ አግባብነቱ እንዲሁም ለአገሪቱ አሳማኝ ጠቀሜታ የሚያስገኝ መሆኑን እና ሌሎች ቁልፍ ጉዳዮችን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል፡፡ ከቦርዱ የመግአ ፕሮጀክቶች የማጽደቅ ኃላፊነትና ስልጣን ጋር በተያያዘም በፕሮጀክቱ ትግበራ ወቅት ቀደም ሲል በቦርዱ ከጸደቀው የፕሮጀክቱ አወቃቀር እና ይዘት አንፃር በመግዓ አወቃቀሩ ላይ ትርጉም ያላቸው ለውጦችን ማስተናገድ በሚያስፈልግበት ጊዜ ቦርዱ የተጠየቀውን ለውጥ መርምሮ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቦርዱ በመግአ አግባብ ፕሮጀክቶችን እንዲተገብሩ የተፈቀዳላቸው መንግስታዊ መ/ቤት ወይም መንግስታዊ የልማት ድርጅት በውል የተለዩ ፕሮጀክቶችን በመግአ ስልት እንዲተገብሩ ትዕዛዝ ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

የቦርዱ ሰብሳቢ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር ሲሆኑ የተለያዩ አግባብነት ያላቸው ሚኒስትሮች፣ የመንግስት መ/ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች እንዲሁም የግል ዘርፍ አባላት የዚሁ ቦርድ አባላት ይሆናሉ፡፡

ተዋዋይ ባለስልጣን እና ለተመረጠው ፕሮጀክት ቀጥተኛ አግባብነት ያላቸው ተቋማት የበላይ ኃላፊዎች እንደፕሮጀክቱ ሁኔታ በቦርዱ ስብሰባዎች ላይ ተሣታፊ ይሆናሉ፡፡ ቦርዱ የተዋዋይ ባለስልጣንን ፍላጎት ብቻ ሳይሆን የአጠቃላይ የመንግስትን ፍላጎት ይወክላል፡፡ ተግባሩን በሚያከናውንበት ጊዜም በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ውስጥ በሚደራጅ የመግአ ማስተባበሪያ ክፍል ይታገዛል፣ ይህ የመግአ ማስተባበሪያ ክፍልም በሴክሬታሪያትነት ያገለግላል፡፡

## ሰ. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

ፕሮጀክቶች በመግአ ስርዓት እንዲቀረጹ እና እንዲተገበሩ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ የመግአ ማዕቀፍ ባለቤት እንደመሆኑ መጠን፣ በመግአ ማስተባበሪያ የሥራ ክፍል እየታገዘ ለተሳካ የፕሮጀክቶች አቀራረጽ፣ ዝግጅት፣ የግዥ ሂደት እና አፈጻጸም ኃላፊነት አለበት፡፡

የእያንዳንዱን የመግአ ፕሮጀክት አተገባበር አስመልክቶ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የሚከተሉት ቁልፍ ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

- አንድ ፕሮጀክት በመግአ ስልት ውስጥ መታቀፍ መቻሉን ለማረጋገጥ ከብሔራዊ ፕላን ኮሚሽን ጋር በመተባበር የመግአ ፕጀክቶችን ዝርዝር እና ቅደምተከተል በማዘጋጀት ለመግዓ ቦርድ አቅርቦ ያስወስናል፡፡ የዚህ ኃላፊነት ዋና ጥቅሙ አንድ ተዋዋይ ባለስልጣን ዝርዝር ጥናት ከማካሄዱና ከፍተኛ ወጪ ከማውጣቱ በፊት በመግአ ለመተግበር የሚታቀዱ ፕሮጀክቶችን አስመልክቶ ስለሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት በቂ ግንዛቤ እንዲያዝ እንዲሁም ለመግአ ፕሮጀክቶች ዝግጅት የሚያስፈልግ የጥናት እና መሰል ወጪዎች በቅድሚያ እና በጥንቃቄ እንዲጤንና እንዲወሰን ማስቻሉ ነው፣

- ለመግአ ፕሮጀክቶች የሚሰጡ የመንግስት ድጋፎችን ወይም በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ኃላፊነት ውስጥ የሚወድቁ ማበረታቻዎችን ያጸድቃል፡፡

  በዚህ ብቻ ሳይገደብ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስልጣን ክልል ውስጥ ባሉ ማናቸውም ጉዳዮች ሊኖር በሚገባው የመንግስት ድጋፍ እና ተሳትፎ ላይ ይወስናል፡፡ ከሁሉም ጎልቶ የሚወጣው ተዋዋይ ባለስልጣኑ በውል መሰረት መወጣት ያለበትን ግዴታ መወጣቱን ለማረጋገጥ ዋስትና ሲጠየቅ ይህንን ዋስትና የመስጠት ኃላፊነት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊነት ነው፡፡

- የመግአ ቦርድን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

## ሐ. የመግአ ማስተባበሪያ የሥራ ክፍል

የመግአ ማስተባበሪያ የሥራ ክፍል ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሆኖ የሚቋቋም አካል ሲሆን የመግአን የትግበራ ስልት በመቅረጽ፤ የአዋጭነት ጥናት እና የጨረታ ሰነድ በማዘጋጀት እንዲሁም የግዢው ውል እንዲፈረም በማድረግ ረገድ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል፡፡ ማስተባበሪያው እነዚህን ስራዎች በሚያከናውንበት ጊዜ ከተዋዋይ ባለስልጣን ጋር የቅርብ ምክክር ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የዚህ ማስተባበሪያ ዋነኛ ግብ የመግአ ፕሮጀክቶችን በመቅረጽ፣ በማዘጋጀት፣ በማጫረት እና በመፈጸም ረገድ በአጠቃላይ በሀገሪቱ መልካም ልምድ እንዲዳብር እና ወጥነት ያለው አሰራር እንዲሰፍን ማድረግ ነው፡፡ በአጭሩ የመግአ ማስተባበሪያ ኃላፊነቶች የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የመግአ ማዕቀፉን በሚቀርጽበት እና በሚያስተዳድርበት ሂደት ሁሉ ቴክኒካል የሆኑ ሥራዎችን በመፈጸምና በማስተባበር የደጋፊነት ሚና መጫወት፤
- የመግአ ፕሮግራም እና ተጨባጭ ፕሮጀክቶች በሚዘጋጁበት ወቅት አስፈላጊ ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት እንዲሁም የማስተባበር ሥራ ማከናወን፣
- የአዋጭነት ጥናት ማካሄድ፣ የተዘጋጁ የአዋጭነት ጥናቶችን መመርመር፣ የጨረታ ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ የጨረታ ሂደቶን መምራት፣ የውል ሰነዶችን ማዘጋጀት፣ ከግል ተዋዋይ ወገን ጋር የሚደረጉ ድርድሮችን መምራት፣ በዚህም ሂደት
- ለገንዘብ ተመጣጣኝ ዋጋ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶችን መለየት እና መተንተን፣
- የመግዓ የጨረታ ሂደትን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ የጨረታ ዶክመንቶች ዝግጅት፣ ድርድር፣ የውል ዶክመንቶች ዝግጅት፣ ወዘተ መምራትና ማስተባበር፣ በዚህም ሂደት የተዋዋይ ባለስልጣን እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት የተሟላ ተሣትፎ መኖሩን ማረጋገጥ፣
- ተዋዋይ ባለስልጣናት የመግአ ፕሮጀክቶችን በሚቀርጹበት፣ በሚፈጽሙበት እና በሚቆጣጠሩበት ሂደት ድጋፍ መስጠት፣
- የመግአ ቦርድ የቀረቡለትን ፕሮጀክቶች በሚገመግምበት እና በሚያጸድቅበት ሂደት ቴክኒካዊ ድጋፍ መስጠት፤

- ስለመግአ ፕሮግራም መረጃዎች በማሰባሰብ ለህዝብ ማድረስ በአጠቃላይ ስለ መግአ የተገኙ ልምዶች እና ምርጥ ተሞክሮዎች በስፋት እንዲሰራጩ ማድረግ፤
- ለመግአ አተገባበር የሚያስፈልግ አገር አቀፍ አቅም እንዲገነባ ለማድረግ እንዲቻል ተቋማዊ አደረጃጀቶችን፣ የአሠራር ሂደቶችን፣ ዝግጁነትና ክፍሎችን ለማጎልበት የሚረዱ ፕሮግሞችን በመቅረጽ በሥራ ላይ ማዋል፣
- የግሉ ዘርፍ በመሰረተ-ልማት አቅርቦት ላይ ያለው ተሳትፎ እንዲጎለብት ለማበረታታት የሚያስችሉ ሥራዎችን ማከናወን ናቸው፡፡

የመግአ ማስተባበሪያ ክፍል የተቀመጡለትን ኃላፊነቶች በብቃት ይወጣ ዘንድ በቴክኒካዊ ችሎታ፣ በህግ ዕውቀት እና በፋይናንስ ሙያ ዕው ቀት፣ ክህሎት እና ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ያስፈልጉታል፣ ይህንንም ለማሟላት ይሰራል፡፡ ጠንካራ ተቋማዊ አቅም መገንባት በአጠቃላይ ለመግአ ፕሮጀክቶች እና ለፕሮግራሙ ስኬት ያለውን የላቀ ትርጉም በመረዳት ከፍተኛ አቅም ያላቸውን ባለሙያዎች መሳብና በቅጥር ለረጅም ጊዜ ማቆየት ወሳኝነት አለው፡፡ እነዚህን በሙያቸው የዳበሩ ባለሙያዎችን ለመቅጠር መንግስት አስፈላጊውን ሁሉ ያመቻቻል፡፡ በተጓዳኝ ወጣት ባለሞያችን ከሰለጠኑና ልምድ ያላቸው ባለሞያዎች ጋር በማቀናጀት አገር አቀፍ አቅምና ቀጣይነት እንዲኖር ይሰራል፡፡ ከዚህ ባሻገርየመግአ ፕሮጀክቶች ዝግጅት፣ የጨረታ ሂደት፣ የኮንትራት አስተዳደር እንዲሁም አጠቃላይ አፈፃፀምና ክትትል ውስብስብ ስለሆነ ሥራዎቹ በውጭ አማካሪዎች እንዲታገዙ ይደረጋል፡፡

## ሠ. ተዋዋይ ባለስልጣን

ተዋዋይ ባለስልጣን ማለት በመግአ እንዲከናወን የሚፈለገውን የህዝብ አገልግሎት በህግ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ሲያቀርብ የቆየ ተቋም ወይም እንዲያቀርብ የሚጠበቅበት ተቋም ማለት ነው፡፡ ተዋዋይ ባለስልጣን የፕሮጀክት ባለቤትነት ያለው በመሆኑ ለፕሮጀክት ቀረጻ፣ ዝግጅት፣ የጨረታ ሂደት እና አፈጻጸም ቀጥተኛ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡ ይህንኑ ኃላፊነት ይወጣ ዘንድ፣ ተዋዋይ ባለስልጣን የመግአ ፕሮጀክትን በመቅረጹ፣ በማዘጋጀቱ፣ በጨረታ ሂደት እና በመፈጸሙ ሂደት ቁልፍ ሚና ይጫወት ዘንድ 'የፕሮጀክት ቡድን' ያቋቁማል፡፡ የተዋዋይ ባለስልጣን የበላይ ኃላፊ የዚህን ቡድን አባላት ይሰይማል፡፡

## የመንግስት ተሳትፎ እና ድጋፍ

የመግአ ፕሮጀክቶችን ከመቅረጽ፣ ከማዘጋጀት፣ ከማጫረት እና ከመቆጣጠር ወሳኝ ተግባራት ባሻገር፣ መንግስት የተለያዩ ዓይነት ድጋፎችን በመስጠትና በቀጥታ በፕሮጀክት አፈጻጸም ላይ በመሳተፍ ተጨማሪ ተግባራት ማከናወን ይኖርበታል፡፡ መንግስት በዚህ ዓይነት የሚያደርገውን ተሳትፎ እና ድጋፍ ቀድሞውኑ በመለየትና በማስታወቅ ለወደፊት የፕሮጀክት ትግበራ ግልፅ እና ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ሆኖም አንዳንዶቹ የተሳትፎ እና የድጋፍ ዓይነቶች ላይ በውል ከመወሰኑ በፊት በጥንቃቄ ላይ የተመሰረተ ግምገማ ማድረግ ይገባል፡፡ አንዱ ወይም ሌላኛው የመንግስት ተሳትፎ ጠቃሚ ነው ወይስ አይደለም ብሎ ለመወሰን የሚቻለውም እያንዳንዱ ፕሮጀክት እና ተሳትፎ በራሱ ሲመረመር ነው፡፡ የመንግሥት ድጋፍ ለመስጠቱ በፊት የሚከተሉት ጉዳዮች በሚገባ ሊመረመሩ ይገባል፡፡

- ለስኬታማ የፕሮጀክት አፈጻጸም ምን ዓይነት የመንግስት ተሳትፎ እንደሚያስፈልግ፣
- ፕሮጀክቱ እንደሚያስገኝ የሚጠበቀም የጥቅም መጠን የዚህን ዓይነት የመንግሥት ተሳትፎ እንዲኖር የሚያስገድድ መሆኑን፣
- የሚመረጠው የአቀራረብ ስልት ተግባራዊ እንዳይሆን የሚከለክሉ እጥረቶች እና መሰናክሎች ስለመኖራቸው፣

የመግአ ማዕቀፍ መንግስታዊ ተሳትፎ ሊኖር የሚችልበትን አግባብ እንዲሁም ድጋፎች ሊሰጡበት የሚችልባቸውን ሁኔታዎች ለይቶ ያሣያል፡፡ በአጠቃላይ መንግስት ድጋፍ የሚያደርግባቸውና የሚሳተፍባቸው መንገዶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- **ለፕሮጀክቶች አፈጻጸም የሚያስፈልግ የማመቻቸት ድጋፍ**

የመግአ ፕሮጀክቶች በረዥሙ ቆይታቸው የተለያዩ መንግስታዊ አካላትን ያሳትፋሉ፡፡ ተዋዋዩ ባለስልጣን ወይም በአጠቃላይ መንግስት አንድ ፕሮጀክት የሚያስፈልጉትን የተለያዩ ድጋፎች እንዲያገኝ በማመቻቸት እንዲሁም በመግአ ዘመኑ ሁሉ እንዲቀርቡ እገዛ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በዚህ መንገድ ጊዜ እና ወጪ መቆጠብ የሚቻልበት ዕድል ከመፈጠሩም በላይ የግል ባለኃብቱ በውሉ ዘመን ሁሉ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ለመወጣት በትጋት እንዲሰራ ያበረታታዋል፡፡

- **በአይነት የሚደረግ ድጋፍ**

ይህ የድጋፍ ዓይነት የፕሮጀክቶችን የተሳለጠ አፈጻጸም ለማረጋገጥ ገንዘብን የማይጨምር ድጋፍ ማድረግን የሚመለከት ነው፡፡ ይህም መሬት ማቅረብን እንዲሁም የፕሮጀክቱን አተገባበር ለማቃለል የሚጋግዙ ድጋፎችን ይጨምራል፡፡ የገቢ ግብር እና ሌሎች የፊስካል ማበረታቻዎችን መስጠትም በዚህ ርዕስ ሥር ይካተታል፡፡ ይሁንና በዚህ መልክ የሚደረግ ድጋፍ የአገሪቱ የህግ ማዕቀፍ በሚፈቅደው መሠረት ሊሰጥ የሚገባው ሲሆን በተለይም በአገሪቱ የኢንቨስትመንት ህግ መሠረት ሊፈጸም ይገባል፡፡

- **የፕሮጀክት ኢንቨስትመንት**

የመግአ ፕሮጀክት የሚያስፈልጋቸውን ፋይናንስ በተሟላ ሁኔታ ማግኘት እንዲችሉ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ መንግስት አክሲዮኖችን በመግዛት ወይም ብድር በመስጠት ሊሣተፍ ወይም ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል።

- **የካፒታል ድጋፍ**

በተለይ በፕሮጀክት ዝግጅት ሂደት ወቅት መንግሥት ለመግአ ፕሮጀክቱ የሚሰጠው የድጋፍ አይነት ሲሆን መንግሥት ይህን ማድረግ የሚፈልግበት ምክንያት አገልግሎቱ መቅረብ ሲጀምር የግል አጋሩ ለአገልግሎቱ የሚያስከፍለው የአገልግሎት ክፍያ ወይም ታሪፍ ለህብረተሰቡ ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ እንዲቀርብ ለማስቻል ነው፡፡ በተጨማሪም የዚህ ዓይነት ድጋፍ የግል አጋሩን የፋይናንስ አቅርቦት ለማሟላት የሚያግዝ ይሆናል፡፡

- **በውል መሰረት የሚፈፀም ክፍያ**

በውሉ ዘመን ከፕሮጀክቱ ጋር በተዛመደ መንግስት ቀጥታ ለሚያገኘው አገልግሎት በገባው የውሉ ግዴታ መሰረት ክፍያ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

- ## ብድር ለማግኘት የሚደረግ ድጋፍ

ተዋዋይ ባለስልጣን በውሉ በገባው ግዴታ መሰረት እንደሚወጣ በዋስትና መልክ ማረጋገጥ የግድ የሚሆንበት ወቅት ሊኖር የችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ባለስልጣኑ በስምምነት የገባበትን ግዴታ እንደሚወጣ፣ ይህ ካልሆነ ግን መንግሥት የተዋዋይ ባለስልጣኑን ኃላፊነት እንደሚወስድ ለማረጋገጥ መንግስት ዋስትና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## የመግዛ ሂደት

## ሀ. የመግዛ ፕሮጀክቶችን መለየት

ለመግአ የሚሆኑ ፕሮጀክቶችን መለየት ለተዋዋይ ባለስልጣን የመደበኛ ስራ አካል እና የመሰረተ-ልማት ዕቅድ አንዱ አካል ነው፡፡ እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት ጉዳይ ቢኖር የመግአ ፕሮጀክቶች የሚመረጡት ከነዚሁ በመደበኛ የተዋዋይ ባለስልጣኑ ዕቅድ ከተዘረዘሩት እና ቅድሚያ ይሰጣቸዋል ከሚባሉት ፕሮጀክቶች መካከል እና ከነዚህም ውስጥ ከግል ዘርፍ አጋር ጋር ቢሰሩ የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ ከሚባሉት ውስጥ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ጊዜም የመግአ ማስተባበሪያ ክፍል በመግአ ስልት ቢከናወኑ የተሻለ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ብሎ ሲያምን ለተዋዋይ ባለስልጣን የፕሮጀክት ሃሳቦችን ሊያቀርብ ይችላል፡፡ በማናቸውም ሁኔታ ቢሆን የመግአ ፕሮጀክቶች ቀድመው በይፋ 'ለመግአ የታጩ' ተብለው አግባብነት ባለው ባለስልጣን መሰየም ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ማለት ለመግአ ፕሮጀክቶች ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተቀመጡት ፖሊሲዎችና ስርዓቶች ለታጩት ፕሮጀክቶች ጥቅም ላይ እንደሚውሉ እንደ ማረጋገጥ ይቆጠራል፡፡ የመግአ ፕሮጀክቶችን የመምረጡ በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር አስተባባሪነት የሚከናወን ሲሆን የፕሮጀክቶቹ ዝርዝር ለቦረዱ ቀርቦ ማጽደቅ ይኖርበታል፡፡ የፕሮጀክት የአዋጭነት ጥናት እና መዋቅራዊ ዝግጅት ለማከናወን በልዩ ሁኔታ በጀት የተመደበ እንደሆነ ደግሞ የአንድ ፕሮጀክት ለመግአ መታጨት ለጥናት ከዚሁ በጀት እንዲጠቀም እንደመፍቀድ የሚቆጠር ነው፡፡

## ለ. የፕሮጀክት አዋጭነት እና አደረጃጀት

በተዋዋይ ባለስልጣን የሚቋቋመው የፕሮጀክት ቡድን አስፈላጊ የሚባሉትን የአዋጭነት ጥናቶች ያካሂዳል፡፡ ይህም ጥናት ቢያንስ የቴክኒክ፣ የህግ እንዲሁም የፋይናንስ ትንተናዎችን ማካተት ይኖርበታል፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ ትንተናዎች በተለያዩ አማራጮች የካፒታል እና የመደበኛ ወጪዎች ትንበያን በማካተት የሚዘጋጅ ሲሆን የጥናቱ ውጤት በፕሮጀክት አወቃቀር ዝግጅት ወቅት እንደግብዓትነት ያገለግላል፡፡ የፕሮጀክት አወቃቀር የሚከተሉትን ጉዳዮች ማካተት ይኖርበታል፡፡

- በአወቃቀሩ ውስጥ የተካተተው የመንግስትና የግል ተዋዋይ ወገኖች የሚኖሩባቸውን ኃላፊነቶች፣

- እያንዳንዱ ተዋናይ ወገን ኃላፊነት የሚወስድበትን የስጋት ዓይነትና መጠን እንዲሁም ከመንግስት ተዋዋይ ወደ ግል ተዋዋይ የሚተላለፍበት አግባብና መንገድ፣
- የሚፈለገውን የመንግስት ተሳትፎ እና ድጋፍ ማካተት ያስፈልጋል፡፡

በፕሮጀክት የመለየት ሥራ እና የአዋጭነት ጥናት ተዋዋይ ባለስልጣኑ በዚህ ፖሊሲ መሠረት ለመግአ መምረጫ ሆነው የተለዩ መመዘኛዎች እና መስፈርቶች መሟላታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

## ሐ. የመግአ ፕሮጀክት አወቃቀርን ማጽደቅ

በቀረበው የፕሮጀክት አደረጃጀት መሰረት እና በመግአ ማስተባበሪያ ክፍል እየታገዘ የመግአ ቦርድ የራሱ የሆነ ግምገማ ያካሂዳል፡፡ ይህ ግምገማ ፕሮጀክቱ ለምዘና የተቀመጡትን መስፈርቶች እስከ ምን ድረስ እንዳሟላና መንግስት ክፍያዎችን ጨምሮ ሌሎች ግዴታዎችን ለመወጣት ያለው አቅም እና ዝግጁነት እንዲሁም ከፕሮጀክቱ የስጋት ሁኔታ ውስጥ መንግስት ኃላፊነት የሚወስድበትን አግባብና መጠን መመርመርን ያካትታል፡፡ የመግአ ቦርድ የፕሮጀክቱን አወቃቀር በተመለከተ የማጽደቅ ውሳኔ በሰጠ ጊዜ ለፕሮጀክቱ በቀረበው አወቃቀር ፕሮፖዛል መሰረት መንግስት ድጋፉን ለመስጠት እንደወሰነ የሚቆጠር ይሆናል፡፡ በሌላ አባባል የፕሮጀክቱን የፋይናንስ አንደምታ እና ከመንግስት የሚጠበቀው ድጋፍ ወይም ተሳትፎ ከወዲሁ መንግስት ተቀብሏል ማለት ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በመግአ ስልት እንዲከናወን ውሳኔ ከተላለፈ በኋላ የመግአ ማስተባበሪያ ክፍል የግል ዘርፍ አጋር የማፈላለግ ስራን መስራት ይጀምራል፡፡

## መ. የግል ዘርፍ አጋርን መምረጥ

ለመግአ ግዢ አፈጻጸም በተቀመጠው ስርዓት መሰረት የመግአ ማስተባበሪያ የግል አጋርየመምረጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ መረጣው ግልጽነት እና ውድድር ባለበት የጨረታ ሂደት መሰረት የሚካሄድ ሆኖ በተጫራቾች ከቀረቡት ፕሮፖዛሎች ውስጥ ለአገሪቱ የተሻለ የላቀ ጥቅም ይሰጣል የሚለውን ጥያቄ በመመለስ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡ የተጨባጭ ፕሮጀክቶች ባህርያት ሊለያይ የሚችል ቢሆንም፤ የመግአ የግዢ ሂደት አብዛኛውን ጊዜ የቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ስርዓት ይኖረዋል፡፡ ይህንን ተከትሎ በቅድመ ብቃት ማረጋገጫ ስርዓት የተመረጡት ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ ሞልተው እንዲያቀርቡና እንዲወዳደሩ ይጋበዛሉ፡፡ በዚህ የጨረታ ምዕራፍ የመግአ ረቂቅ ውል ለግምገማ ይላካል፡፡ በተላከው ረቂቅ ውል ላይ ቅድመ ማጣሪያን ያለፉ የግል ድርጅቶች አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡ ይህ ከሆነ በኋላ ነው የውል ረቂቁ የመጨረሻ ዶክመንት ለተጫራቾች ስርጭት ዝግጁ ነው ተብሎ የሚወሰደው፡፡ ለሁሉም ተጫራቾች ከጨረታ ሰነዶች ጋር የውሉን ናሙና አያይዞ በመበተን ተጫራቾች እኩል መረጃ እንዲያገኙ ማድረግ የግድ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን በስምምነት ድርድር ሂደት ውስጥ በመግአ ፕሮጀክት የስጋቶች ሁኔታ ድልድልም ሆነ ለመንግስት ወይም ከመንግስት በሚኖረው የገንዘብ ፍሰት ላይ ትርጉም ያላቸውን ለውጦች ማስተናገድ የግድ ከሆነ የፕሮጀክቱ ሰነድ በድጋሚ ለመግአ ቦርድ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

በራስ ተነሳሽነት የመግአ የፕሮጀክት ሃሳብ ከግል ዘርፍ ወገኖች የሚቀርብበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ በራስ ተነሳሽነት የሚቀርቡ የፕሮጀክት ሃሳቦች ወደ መግአ ሥርዓት ከማስገባት ጋር በተያያዘ ውድድር ማስፈን አስፈላጊ ስለሚሆን እነዚህ የፕሮጀክት ኃሣቦች በምን መንገድ መስተናገድ እንዳለባቸውና በአጠቃላይ የመግአ ግዢ ስርዓትና አማራጮች ምን እንደሚመስሉ በመግአ ማዕቀፍ ተብራርተው ይቀርባሉ፡፡

## ሠ. አሸናፊውን መምረጥ እና ስምምነትን መፈረም

አሸናፊው ተጫራች ከተለየ በኋላ የመግአ ማስተባበሪያ የሥራ ክፍል የጨረታ ሂደቱን አጠናቆ ተዋዋይ ባለስልጣኑ ውሉን ከመፈረሙ በፊት የመግአ ቦርድ የመጨረሻ ውሳኔን መስጠቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ቦርዱ የጨረታውን ውጤት ሲያጸድቅ የመግአ ማስተባበሪያ ክፍል አሸናፊውን ወገን በይፋ ያሳውቃል፡፡ ይህንን ተከትሎ ከተዋዋይ ባለስልጣኑ ጋር ውል ለመፈራረም አስፈላጊው ዝግጅት ያደርጋል፡፡ ምንም እንኳን አሸናፊ ከተለየ በኋላ ድርድር የሚካሄደው በጣም ውስን በሆኑ አጋጣሚዎች ቢሆንም (መካሄድም ካለበት)፤ የስምምነት ረቂቁን ማስተካከል ወይም ማረም የግድ የሚሆንበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይህም በተለይ ሊሆን የሚችለው የመግአ ፕሮጀክት ወጪ በውጭ ብድር የሚሸፈን በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡ አሁንም ከላይ እንደተገለጸው፤ የስጋት ሁኔታዎች ድልድል እና የገንዘብ ፍሰት ላይ ትርጉም ያለው ለውጥ የሚፈጠር ከሆነ እንደገና ለመግአ ቦርዱ አስቀርቦ ማስወሰን የግድ ይሆናል፡፡ ለዚህ ለውጥም ተጨማሪ የቦርዱ ስምምነት ከተገኘ፤ የመግአ ማስተባበሪያ የሥራ ክፍል እና ሌሎች ፈራሚ የመንግስት አካላት የመግአን ስምምነት ለመፈረም እና ፕሮጀክቱን ለማስጀመር የሚያስችል ፈቃድ አግኝተዋል ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተዋዋይ ባለስልጣን የግል ዘርፍ አጋሩ በፋይናንስ ረገድ ከሌሎች ወገኖች ጋር ሙሉ ስምምነት ላይ እንዲደርስ ያግዛል፡፡

## ረ. ትግበራ እና ክትትል

የተዋዋይ ባለስልጣን ተግባርና ኃላፊነት በፕሮጀክት ትግበራ ወቅትም ይቀጥላል፡፡ ተቋሙ ከግል አጋሩ ጋር በተገባው ውል መሠረት የኮንትራት አስተዳዳር ሥራ ያካሂዳል፡፡ በትግበራ ምዕራፍ የግል ዘርፉን የስራ አፈጻጸም ይገመግማል፡፡ የተነደፈው ፕሮጀክትና የትግበራ ስልት የአገልግሎት የአቅርቦት ፍላጎቶችን ምን ያክል እንዳረካም መገምገም እና መከታተል ይኖርበታል፡፡ ይህንን ለማሳለጥ፣ ፕሮጀክቱን የነደፉ እና ያዘጋጁ የፕሮጀክት ቡድን አባላት የመግአ ስምምነቶችን እንዴት ማስተዳደር እና መከታተል እንደሚቻላቸው የሚያብራራ የስራ መመሪያ ያዘጋጃሉ፡፡ በዚህ መመሪያ ውስጥ በውል የሰፈሩት ቀጣይነት ያላቸው እንደ የፋይናንስ ግዴታዎችን መወጣት እና የስራ አፈጻጸምን መከታተል የመሳሰሉ የመንግስት ኃላፊነቶች በዝርዝር ይሰፍራሉ፡፡ እነዚህ የውል አስተዳደር መመሪያዎች ለፕሮጀክት ቡድን እና ቀጥሎ ለሚደራጁት ቡድኖች በፕሮጀክቱ የቆይታ ዘመን ውሎችን እንዴት መከታተል እና መቆጣጠር እንዳለባቸው ቋሚ ማጣቀሻ ሆነው ያገለግላሉ፡፡